አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር: 13/ 2012 ዓ.ም
Issue No. 13 2020

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter

በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by Marketing & Communication Directorate

GET IN TOUCH

8980
+251 11 55 70 167
www.awashbank.com


# በዚህ ዕትም


የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት ........ 1
አዋሽ ባንክ በጅማ ከተማ ያስገነባውን ዘመናዊ ህንፃ አስመረቀ ........ 3
የእህት ኩባንያዎቹ 25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓል አከባበር ........ 4
አዋሽ ባንክ በብድር ላይ የሚከፈለውን የወለድ ምጣኔ እስከ 4.5 በመቶ ዝቅ እንዲል አደረገ ........ 5
የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ተካሄደ ........ 6
አዋሽ ባንክ ሙሉ ለሙሉ ወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት የሚሰጥበት ቅርንጫፍ ከፈተ ........ 7
የፈርጦቹ ጉዞ ........ 14


# In This Issue


**Awash Bank and Amref Health Africa Signed Partnership Agreement** ........ 7
**Awash Bank and USAID Signed Partnership Agreement** ........ 8
**Awash Bank to construct new building** ........ 9
**Financial takeaway** ........ 12
**Proverbs** ........ 14





**አቶ ፀሐይ ሽፈራው**
የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

# የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መልዕክት

## አዋሽ ባንክን በስኬት ማማ ላይ ያኖሩት ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል ! !

እ.ኤ.አ. በወርሃ ግንቦት 1991 ዓ.ም በአገራችን የተፈጠረውን የመንግስት ለውጥ ተከትሎ ተግባራዊ በተደረገው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ወደ ባንኪንግ ክፍለ ኢኮኖሚ በመግባት አዋሽ ባንክ የመጀመሪያውና ፈር ቀዳጅ የሆነ የግል ባንክ ነው፡፡

ጠንካራና ተመራጭ የህዝብ ባንክ የመሆን ራዕይ ሰንቆ የተነሳው አዋሽ ባንክ ላለፉት 25 ዓመታት ከወቅቱ ጋር እራሱንና የአገልግሎት አሰጣጡን እያዘመነ በመሄድ በሁሉም የሥራ ዘርፎች ከፍተኛና ተከታታይነት ያለው ዕድገት አስመዝግቧል፡፡

ቀድሞ ወደ ዘርፉ በመግባት የመጀመሪያው የግል ባንክ እንደሆነ ሁሉ በአገራችን የግል ባንኮች ታሪክ ከብር አንድ ቢሊዮን በላይ ዓመታዊ ትርፍ ያስመዘገበ የመጀመርያው የግል ባንክ ከመሆኑም ባሻገር ባሳለፍነው በጀት ዓመት ብር 3.3 ቢሊዮን ዓመታዊ ትርፍ በማግኘት በኢትዮጵያ የግል ባንኮች ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አንፀባራቂ ውጤት አስመዘግቧል፡፡

ይህ አመርቂ ውጤት የተመዘገበው በወቅቱ 25ኛ ዓመት የምስረታ በዓላችንን በምናከብርበት ዋዜማ ላይ መሆኑ ደግሞ ደስታችንን እጥፍ ድርብ አድርጎታል፡፡

አዋሽ ባንክ በሂሳብ ዓመቱ ሁለት ታላላቅ ግቦችን ለማሳካት ሲንቀሳቀስ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ለቪዥን 2025 ስኬት ያስቀመጠውን ግብ ለማሳካት በሁሉም ዘርፎች ያቀደውን ለመተግበር ሰፊ እንቅስቃሴ ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ከእህት ኩባንያው አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. ጋር በጥምረት 25ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን በድምቀት ለማክበር ዝግጅት ሲያደርግ የነበረበት የሂሳብ ዓመት ነበር፡፡

በአስተማማኝ ፋይናንስ፣ በቀልጣፋ አገልግሎትና በሰፊ ህዝባዊ መሰረት ላይ ፀንቶ በመቆም የሚታወቀው አዋሽ ባንክ

ወደሚቀጥለው ገጽ ተዘዋውሯል...



በብልህ አመራሮቹ በሳልና ወቅታዊ ውሳኔ ሰጪነት እንዲሁም በሠራተኞች ትጋትና ብቃት በመታገዝ የነበሩትን ፈታኝ ነገሮችን ወደ መልካም አጋጣሚ በመለወጥ የሂሳብ ዓመቱን በታላቅ ስኬት አጠናቋል፡፡

ከ2017/18 ሂሳብ ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ70 በመቶ ወይም የብር 1.38 ቢሊዮን ጭማሪ አሳይቷል ፡፡

የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ከብር 2.94 ቢሊዮን የብር 1.44 ቢሊዮን ጭማሪ በማሳየት ወደ ብር 4.4 ቢሊዮን አድጓል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ለእያንዳንዱ አክሲዮን የሚከፈለው የትርፍ ክፍያ ከብር 543 ወደ ብር 632 አድጓል፤ ይህም በግል የፋይናንስ ተቋማት ታይቶ የማይታወቅ ውጤት ነው፡፡

ከተቀማጭ ገንዘብ አንፃር እ.ኤ.አ በ2017/18 ከነበረበት የ36 በመቶ ዕድገት በማሳየት በ2018/19 የሂሳብ ዓመት መጨረሻ ላይ ብር 62.46 ቢሊዮን ሆኖ ተመዝግቧል፡፡


አጠቃላይ የሀብት መጠንም እ.ኤ.አ በ2017/18 ከነበረበት ብር 55.27 ቢሊዮን በ2018/19 የሂሳብ ዓመት መጨረሻ ላይ ወደ ብር 74.77 ቢሊዮን አድጓል፡፡

ይህም በአንድ ዓመት ብቻ የብር 19.49 ቢሊዮን ጭማሪ የተመዘገበበት ነው፡፡ ባንኩ በበጀት ዓመቱ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰጠው የብድር መጠንም እንዲሁ ከፍተኛ የሚባል ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የብድር መጠኑ በከፍተኛ ሁኔታ ቢጨምርም ባንኩ ጠንካራ አሰራር የሚከተል በመሆኑ የተበላሹ ብድሮች መጠንም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው የአምስት በመቶ በጣም ዝቅ ባለ ደረጃ ከ1.1 በመቶ በታች ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም የባንኩን ጠንካራ የብድር አስተዳደር አመላካች ነው፡፡

በአጠቃላይ ባንካችን በ25 ዓመታት የስኬት ጉዞው በሁሉም ዘርፎች አዳዲስ ድሎችን እየተቀናጀ መሰረቱን በማይናወጥ ፅኑ ዓለት ላይ አኑሯል፡፡

ለዚህም ላለፉት አራት ተከታታይ የሂሳብ ዓመታት መሪነቱን እንደያዘ መቀጠሉ ተጨባጭ ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ውጤት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር የተገኘ ስለሆነ አዋሽ ባንክን በስኬት ማማ ላይ ያኖሩት ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

የሩብ ምዕተ ዓመት የስኬት ጉዞአችን ጠንክረንና ተባብረን ከሰራን የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር ካሰብንበት ለመድረስ እንዳች የሚያስቆመን ኃይል አለመኖሩን ያረጋገጥንበት ነው፡፡ ስለሆንም የባንካችንን ቪዥን 2025 ለማሳካት እንደተለመደው ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለበለጠ ስኬት ለመብቃት መስራት ይጠበቅብናል፡፡



# አዋሽ ባንክ በጅማ ከተማ ያስገነባውን ዘመናዊ ህንፃ አስመረቀ

አዋሽ ባንክ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ከተማ አስተዳደር በ1,930 ሜትር ካሬ ቦታ ላይ ያስገነባውን ባለ ስድስት ወለል ዘመናዊ ሕንጻ አስመረቀ፡፡

ባንኩ ከሚታወቅባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ በተለያዩ የሀገሪቷ ዋና ዋና ከተሞች ሕንጻዎችን መገንባት ነው ያሉት የባንኩ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው፣ አዋሽ ባንክ ከግል ባንኮች የራሱን የዋና መ/ቤት ሕንጻ በማሠራት የመጀመሪያው የግል ባንክ ሲሆን ከአዲስ አበባ ውጪም ባለፉት ዓመታት የራሱን ሕንጻዎች ለመገንባትም ሆነ የተገነቡትን ለመግዛት ሰፊ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ከ12 በላይ የራሱን ህንፃዎች በመገንባት የሀብት መጠኑን ከማሳደግ ጎን ለጎን ለከተሞች ዕድገትም የራሱን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

አዋሽ ባንክ በጅማ ከተማ በአምስት ቅርንጫፎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ያሉት ዋና ስራ አፈፃሚው፣ በዚህች የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ፈርጥ በሆነችው ከተማ ሕንጻ ለመገንባት የተፈለገበት ዋናው ምክንያትም ከተማዋ በአገራችን በንግድ ማዕከልነት ከሚታወቁት ከተሞች አንዷ ከመሆኗም በላይ የባንኩ ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ ከሚካሄድባቸው ከተሞች መካከል አንዷ መሆኗን ጭምር አስረድተዋል፡፡



በሕንጻው ምርቃት ላይ የተደረገ የማርሽ ባንድ ትርዒት

በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የጅማ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ መኪዩ መሐመድ በበኩላቸው ሕንጻው የተገነባበት አካባቢ ለንግድና ለተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ተፈላጊ ሥፍራ መሆኑም የህንፃውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍ ከማድረጉም በላይ ለጅማ ከተማም ልዩ ውበት ይሰጣል ብለዋል፡፡

አዋሽ ባንክ በጅማ ከተማ ሰርቶ ያገኘውን ትርፍ ወደ ሌላ አካባቢ ሳይወስድ በከተማችን በእንደዚህ ዓይነት ልማት ላይ ማዋሉ የሚያስመሰግነው ተግባር ነው ያሉት ከንቲባው፣ ሌሎች በከተማዋ እየሰሩ ያሉ ባንኮችና ልዩ ልዩ ተቋማትም ከዚህ ሊማሩ እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡፡



# የእህት ኩባንያዎቹ 25ተኛ ዓመት የብር ኢዩቤልዩ በዓል አከባበር

የአዋሽ ባንክ እና የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ የተመሰረቱበትን 25ተኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ ክብረ በዓል በተለያዩ ዝግጅቶች አከበሩ፡፡

አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ. እ.ኤ.አ 1991 በአገራችን የገበያ መር ኢኮኖሚ ፖሊሲ መታወጁን ተከትሎ ወደ ፋይናንስ ሴክተር የገቡ የመጀመሪያዎቹ የግል ባንክ እና የመድን ኩባንያ ናቸው ፡፡

አዋሽ ባንክ ስትራቴጂያዊ ግቦችና ዓላማዎቹን ለማሳካት ለደንበኞቹ የተለያዩ የባንኪንግ አገልግሎቶችን በማቅረብ ተደራሽና ተመራጭ የሆነ ባንክ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ እህት ኩባንያው አዋሽ ኢንሹራንስ በአገልግሎት ዘርፉ በርካታ ስራዎችን ላለፉት ሃያ አምስት አመታት ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ባለፉት 25 ዓመታት አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አስተማማኝ የባንክ እና የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን ለህዝቡ በመስጠት ስኬታማ ታሪኮችን አስመዝግበዋል ፡፡

ይህ የስኬት ታሪካቸውም እህት ኩባንያዎቹ ለወደፊት የገቢያ ድርሻ ማስፋቱን ይበልጥ እንዲያጠናክሩ እና በአገልግሎቶቻቸው በህዝቡ ልብ ውስጥ ዘልቆ በመግባትና የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜት ለመፍጠር እንደሚያስችላቸው ታምኖበታል፡፡



**በሥነ-ስርዓቱ ላይ የታደሙ እንግዶች በከፊል**

እህት ኩባንያዎቹ የ25ኛ ዓመት የልደት በዓል ሻማቸውን የለኮሱት ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ባለአክሲዮኖች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አመራሮችና አባላት እንዲሁም የሁለቱም ኩባንያዎች የማኔጅመንት አባላት እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በመከላከያ ሰራዊት የማርሽ ባንድ ትዕይንቶች በመታጀብ ነበር፡፡




**የእለቱ የክብር እንግዳ ዶ/ር ይናገር ደሴ በተገኙበት የተደረገ የኬክ ቆረሳ ሥነ-ሥርዓት**

ጥቅምት 14 ቀን 2012 ዓ.ም በዋናው መ/ቤታቸው መግቢያ በር ላይ ያሰሩትን ቢልቦርድ መርቆ በመክፈት የብር እዮበልዩ በዓላቸውን በይፋ ማክበር መጀመራቸውን ያበሰሩት እህት ኩባንያዎቹ የማጠቃለያና የበዓሉ መዝጊያ ፕሮግራም ህዳር 13 ቀን 2012 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል በደማቅ ሁኔታ አካሂደዋል፡፡

በእለቱ ከተከናወኑ ሥነ-ሥርዓቶች ውስጥ በዋናነት ለተለያዩ ሀገር በቀልና አለም ዓቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ማህበራዊ ሀላፊነትን ከመወጣት አኳያ የብር 20 ሚሊዮን የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን በአዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ውስጥ 25 አመታት ላገለገሉ ሰራተኞች የረጅም አገልግሎት ዕውቅና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

በቀጣይ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተግባራዊ በሚያደርጋቸው የሪፎርም ስራዎች የአዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አመራሮችና ሰራተኞች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እንዳለባቸው የእለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት የብሄራዊ ባንክ ገዥ ዶ/ር ይናገር ደሴ መልክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡



# አዋሽ ባንክ በብድር ላይ የሚከፈለውን የወለድ ምጣኔ እስከ 4.5 በመቶ ዝቅ እንዲል አደረገ

የ27 በመቶ ቦንድ የገዙበትን ገንዘብ ለብድር ቢያውሉት ኖሮ አሁን ብዙ ለመሥራትና እስካሁን ካስመዘገቡትም በላይ ውጤት ለማምጣት ይጠቅማቸው እንደነበር የዘርፉ ባለሙያዎች ትንታኔ ሲሰጡበት ቆይተዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ ይናገር ደሴ (ዶ/ር) የመመርያው መነሳትን በማስመልከት በሰጡት መግለጫ፣ በባንኮች የሚሽከረከረውን የገንዘብ ፍሰት እንዲጨምር ከማድረጉም በላይ የብድር ወለድ ዝቅ እንዲል በማድረግ የግል ባንኮች የጥሬ ገንዘብ እጥረት ሳይገጥማቸው ብድር እንደ ልብ ማቅረብ እንዲችሉ ያግዛቸዋል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ በቋሚነት ለሚጀመረው የመጀመሪያ ደረጃ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነድ ግብይት ላይ ባንኮች እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ታስቦ፣ የ27 በመቶው የቦንድ ግዥው መመሪያ መነሳቱን የባንኩ ገዥ ተናግረዋል። የመመሪያው መነሳትን ተከትሎ በጥቂት ቀናት ውስጥ አዋሽ ባንክ ተነሳሽነት በመውሰድ የማበደሪያ ወለድ ላይ ቅናሽ እንደሚያደርግ በይፋ በመግለጹ ሌሎችም ይህንኑ መንገድ ይከተላሉ የሚል ግምት አሳድሯል።

ባንኩ ኅዳር 16 ቀን 2012 ዓ.ም. ይፋ እንዳደረገው፣ እስካሁን ሲሠራበት የቆየው የብድር ወለድ ምጣኔ ላይ ከ0.5 በመቶ እስከ 4.5 በመቶ ቅናሽ ማድረጉን አስታውቋል።

አዋሽ ባንክ የብድር ወለድ ቅናሽ ማድረጉ በገበያው ውስጥ እየታየ ያለውን የዋጋ ግሽበት በጥቂቱም ቢሆን ለመቀነስ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚችል በማመን የተወሰደ ዕርምጃ እንደሆነ አቶ ደሳለኝ ቶሌራ ገልጸዋል።



አቶ ደሳለኝ ቶሌራ ጋዜጣዊ መግለጫ በሚሰጡበት ወቅት

ባንኩ የወሰደው ዕርምጃ ኢንቨስትመንትን እንደሚያበረታታውና የተቀዛቀዘውን የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚያነቃቃውም ተስፋ ተደርጎበታል።

የባንኩ የንግድ ብድር ኃላፊ አቶ ቶማስ ፍቃዱም በበኩላቸው የወለድ ቅናሽ ከመደረጉ በፊት ጥናት ሲደረግ እንደነበር አስታውሰዋል። ‹‹የትኛውን ወለድ ብንከፍል የትኛው ኅብረተሰብ ይጠቀማል? በማለት ባንኩንም ሆነ ኢኮኖሚውን በማይጎዳ መልኩ ተጠንቶ የተወሰነ ነው›› ብለዋል።



# የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ተካሄደ

ባንኩ የተጠናቀቀውን ሒሳብ ዓመት ክንውን በማስመልከት ይፋ ባደረገው ሪፖርት መሠረት፣ በዋና ዋና የባንክ ሥራ ዘርፎች ውጤታማ እንቅስቃሴ በማስመዝገብ ከግል ባንኮች አኳያ የመሪነት ቦታውን እንዳስጠበቀ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ታቦር ዋሚ ገልጸዋል፡፡



**አቶ ታቦር ዋሚ አመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት**

አዋሽ ባንክ ከፍተኛ አፈጻጸም ካሳየባቸው ክንውኖቹ መካከል የውጭ ምንዛሪ ግኝቱ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከውጭ ንግድ ዘርፍ፣ ከውጭ የሐዋላ አገልግሎት፣ እንዲሁም ከተለያዩ ድርጅቶች ያገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከ918.9 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደሆነ አስታውቋል፡፡ ይህ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከ2010 ዓ.ም. ጋር ሲነፃፀር የ327.2 ሚሊዮን ዶላር ወይም የ55 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡

ባንኩ ያስመዘገበው የውጭ ምንዛሪ መጠን፣ ከኢትዮጵያ የሚላኩ ሸቀጦች የሚያስገኙት ጠቅላላ ገቢም ሆነ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እየቀነሰ በመጣበት ወቅት በመሆኑ፣ ለባንኩ ብቻም ሳይሆን ለኢኮኖሚውም በትልቅ ውጤትነት እንደሚገለጽ የቦርድ ሰብሳቢው አስታውሰዋል፡፡


ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በስተቀር ከተቀሩት የግል ባንኮች መካከል አዋሽ ባንክ አብላጫውን የገበያ ድርሻ መያዙን አቶ ታቦር ተናግረዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር በ2011 ዓ.ም. የባንኩ ሠራተኞች ያላቸውን ዕውቀትና ክህሎት የበለጠ እንዲያሻሽሉ ለማስቻል ከ39 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ሥልጠናዎች እንዲከታተሉ ስለማድረጉም አስታውቋል፡፡

በ2011 ዓ.ም. ሒሳብ መዝጊያ ወቅት አዋሽ ባንክ ያስመዘገበው የ3.34 ቢሊዮን ብር ያልተጣራ ትርፍ፣ ለአዋሽ ባንክ በታሪክ ትልቁ ብቻም ሳይሆን፣ በአገሪቱ የግል ባንኮችም ረገድ ከዚህ ቀደም ያልተመዘገበ ትልቅ የትርፍ መጠን እንደሆነ ያመለከቱት አቶ ታቦር፣ ይህም የትርፍ መጠን በ2010 ዓ.ም. ከተገኘው የ1.96 ቢሊዮን ብር ትርፍ ጋር ሲነፃፀር የ70 በመቶ ወይም የ1.38 ቢሊዮን ብር ጭማሪ የታየበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

አዋሽ ባንክ ያሰባሰበው ተቀማጭ ገንዘብም በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን በሪፖርቱ አመላክቷል፡፡ ወለድ አልባ የባንክ አገልግሎትን ጨምሮ የ2011 ዓ.ም. የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ በ36 በመቶ ወይም በ16.5 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አሳይቷል፡፡ አጠቃላይ መጠኑም 62.5 ቢሊዮን ብር እንደደረሰ አስታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ባንኩ ለተለያዩ ዘርፎች ያሠራጨው ብድርም የ51 በመቶ ጭማሪ በማሳየት 47.3 ቢሊዮን ብር እንደደረሰ አቶ ታቦር አመልክተው፣ በተለይ በመንግሥት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ለወጪ ንግድና ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች የሰጠው ብድር ከፍተኛውን ድርሻ በመያዝ ዕድገት እንዳሳዩ ጠቅሰዋል፡፡

አዋሽ ባንክ ከፍተኛ ጭማሪና ዕድገት ያሳየበት ሌላው እንቅስቃሴ የባንኩ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ሀብት የሚያሳየው የሒሳብ መጠን ነው፡፡ በ2011 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ የ19.5 ቢሊዮን ብር ዕድገት በማስመዝገብ ወደ 74.6 ቢሊዮን ብር ያደገው የባንኩ ጠቅላላ ሀብት በ2010 ዓ.ም 55.3 ቢሊዮን ብር ነበር፡፡

የባለአክስዮኖችን ውሳኔ በተመለከተ የባንኩን ካፒታል እ.ኤ.አ ሰኔ 2020 መጨረሻ ድረስ ብር 6 ሚሊዮን ለማድረስና እ.ኤ.አ ሰኔ 2023 ድረስ ደግሞ ብር 12 ቢሊዮን ለማድረስ የተስማሙ ሲሆን በ14ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት 5 በመቶ ወይንም 300,000 አክስዮኖች ለባንኩ ሠራተኞች ያላቸውን ሃላፊነትና የሥራ ድርሻ መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲሁም የተቀረው ደግሞ ለባንኩ ነባር ባለአክስዮኖች ባላቸው የአክስዮን ድርሻ መሰረት ተደልድሎ እንዲሸጥላቸው ውሳኔ ተላልፏል፡፡



# አዋሽ ባንክ ሙሉ ለሙሉ ወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት የሚሰጥበት ቅርንጫፍ ከፈተ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ  ባንኮች ከመስኮት አገልግሎት ውጪ ራሱን የቻለ የወለድ አልባ ቅርንጫፍ ከፍተው መሥራት እንደሚችሉ ካሳወቀ ወዲህ፣ የተለያዩ ባንኮች ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ብቻ የሚሰጥ ቅርንጫፍ ወደ መክፈት እየገቡ ነው።

አዋሽ ባንክ ኅዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም.  ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የሚሰጥ ቅርንጫፍ አዲስ አበባ ቤተል አካባቢ የባንኩ ከፍተኛ የስራ አመራር አባላትና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በደማቅ ስነስርዓት በመክፈት ለሙስሊሙ የህብረተሰብ  ክፍል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።



ቅርንጫፉ ተመርቆ ሲከፈት

አዋሽ ባንክ የአገልግሎት ዘርፉን በማስፋፋት ለውድ ደንበኞቹ አመቺ በሆነ መንገድ በይበልጥ ተደራሽ ለመሆን ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ሲከውን መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን አሁን የጀመረውንም ወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት በማጠናከር በአዲስ አበባና በተለያዩ የተመረጡ ክልል ከተሞች አገልግሎቱ እንደሚጀመር ለማወቅ ተችሏል።

ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ በሦስት የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም ቦሌ ሚካኤልና በሰባተኛ ቅርንጫፎቻችን ቀደም ሲል በአንድ መስኮት ብቻ ይሰጥ የነበረው ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ለብቻው ወጥቶ የተሟላ አገልግሎት መስጠት በሚችል መልኩ ተደራጅተው ስራ እንዲጀምሩ የተደረገ ሲሆን በበርበሬ ተራ ደግሞ ኪድማ በሚል ስያሜ አዲስ ቅርንጫፍ ከፍቶ ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል።

# Awash Bank and Amref Health Africa Sign a Partnership Agreement

Awash Bank, the leading private bank in Ethiopia and Amref Health Africa, the largest Africa based international non-governmental organization (NGO) signed a long term partnership agreement to work jointly towards improving the health and well-being of Ethiopians, support progress towards Universal Health Coverage (UHC) and collaborate to narrow gender inequity gaps across Ethiopia.




Partnership signing ceremony

As part of this long term partnership agreement and its first initiative working with Amref Health Africa, Awash Bank now provides financial support for the construction of 10 sanitation facilities to be implemented by Amref Health Africa in selected government schools in Addis Ababa.

The project is expected to improve sustainable and equitable access to WASH for more than 20,000 school communities, and will be put

Continued to the next page



into practice immediately up on the signing of the agreement document by both parties. This first intervention appears to be an important commitment to address the sanitation and hygiene problems of school children in their school setting; thereby contribute to the Sustainable Development Goals.

Amref Health Africa, headquartered in Kenya, is the largest Africa based international non-governmental organisation (NGO) currently running programs in over 35 countries in Africa with lessons learnt over 60 years of engagement with governments, communities and partners to increase sustainable health access in Africa. With its Corporate Social Responsibility (CSR) program, Awash Bank, has been contributing a lot to public development programs for the last 25 years. Since its inception, the bank had donated millions of Birr to the vulnerable and marginalized sections of the society.


## Awash Bank and USAID sign Partnership Agreement

The U.S. Agency for International Development (USAID) and Awash Bank have announced a new partnership that will make up to US $6.4 million in financing available to microfinance institutions and small- and medium-sized agricultural businesses in Ethiopia.




Partnership signing ceremony

Awash Bank S.C. was a USAID Development Credit Authority (DCA) partner on two Loan Portfolio Guarantees. The two projects were accomplished successfully without any defaults on loans. Awash Bank, cognizant of the potential of the small and medium-enterprise (SME) segment for the overall development of the nation’s economy, has established the SME Banking operation unit under a Directorate level.



# Awash Bank to construct new building

Awash Bank signed contractual agreement with Rama Construction plc to construct the office building in Addis Ababa around Saris, named as Bulbula building.




Contractual agreement signing ceremony

The building will have 13 floor and expected to be completed within 36 months. The contractual agreement has been signed by Ato Tshehay Seferaw, Awash Bank Chief Executive Officer and Ato Biruk Tedla, Rama Construction Plc Managing Director.

Rama Construction, with more than 20 years experience in construction industry, expected to complete the building with expected quality within a contractual management framework said Ato Tsehay, Awash Bank CEO on the contractual signing ceremony.

The Construction plc, Rama Construction is not only the contractor executing of this contract, but also the corporate customer for the bank and thus will handle the project with sense of ownership, Ato Tsehay added. Ato Tsehay also stressed that, 57 Architects, who handle the consultation issue of the building also work closely with both contractor and client to monitor the progress of the project as per the contract, including quality and time frame.

Rama Construction Managing Director, Ato Biruk Tedla on his part confirmed that, as the Plc is well experienced in the industry, it works hard to meet the contract management principles in all aspects.

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River

# Use your cards




MasterCard VISA UnionPay 银联

**@**
**Awash ATMs and POS terminals!**

*We are determined to simplify your way of doing business!*

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# ከአዋሽ ይቀበሉ!ያሸንፉ!! 8ኛው ዙር




## 1ኛ ዕጣ አንድ አይሱዙ ዘመናዊ የጭነት መኪና



2ኛ ዕጣ - ኤል ኢዲ ቴሌቭዥኖች



3ኛ ዕጣ - የዉሃ ማጣርያዎች



4ኛ ዕጣ - ተንቀሳቃሽ
የስልክ ቀፎዎች

## ከታህሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ

PayPal · Western Union Money Transfer · Dahabshiil · MoneyGram · Xpress Money · Ria · EzRemit · Moneytrans · AME Asgori Money Express · Trans-Fast · mfi · Doha Bank · Send Exchange · Money Exchange · Dubai Remit · Al Ansari Exchange · worldremit · Awinetaa



# Digital Financial Services: Lessons from Kenya

With a population of 47 million, Kenya is the economic, financial and transport hub of East Africa. Despite this, its population is largely agrarian with three-quarters living in rural areas and 61 percent being employed at least part time in agriculture, mainly as smallholder farmers. Agriculture remains the backbone of the economy, providing one third of the GDP. Recently, Nairobi has emerged as a fintech hub, with its 'silicon savannah' status based on opportunities arising from the success of its Digital financial Services (DFS) sector.

Financial inclusion is high, with 82 percent of adults having an account of some form in 2017, largely driven by the impact of mobile wallets. The number of Kenyans with a formal bank account has also grown significantly over this period. Excluding bank/MNO savings and loan partnerships, the number of banked customers has grown steadily in the last ten years, suggesting that the introduction of mobile wallets has had a synergistic effect.

A wide range of services are available via mobile wallets. M-Shwari micro-savings and loans based on usage of both the mobile wallet and mobile network have been available since 2012, and have proven to be extremely popular both in Kenya and other markets where the model has been copied. However, the biggest breakthrough that the Kenyan market has achieved since the launch of DFS is probably the wide-scale acceptance of M-PESA for retail (merchant) payments.


## Success factors in Kenya

CNN, business editors Kai Keller & Petter Van- ham believes that the regulatory environment played a key role for the success of DFS in Kenya. When Safaricom was launched in 2007, the regulator offered Safaricom a 'no objection' letter that allowed the company to innovate, to pilot test its service without the confines of strict regulation.

Nowadays, one would be hard pressed to find a regulator as open to this approach as the Central Bank of Kenya was. Higher education levels and literacy rates, coupled with good infrastructure, allowed Safaricom to successfully launch its service. To date, M-PESA has 18.2 million mobile money subscribers and almost 80,000 agents across Kenya, making it the most successful DFS deployment the world has seen. Besides, the Kenyan market was ready. Prior to M-PESA, there were limited means of transacting and conducting payments. Previous methods of doing bus transfers were unreliable, and using commercial banks was expensive and out of reach for the low-income market segment.

## What lessons can be learned from Kenya?

It is estimated that widespread use of digital finance has the potential to boost the annual GDP of emerging economies by US$ 3.7 trillion by 2025 and two-thirds from increased productivity of larger businesses and government. The question is how do we get there? To get an idea of where the future may take us, it is helpful to learn from Kenya who has the largest and most successful mobile money sector in Africa and has



consistently led the continent both in scale.

However, the lessons that emerge from this blossoming industry may be helpful to keep in mind when considering the long journey that other markets are about to embark on as they build DFS businesses. Providers will need to consider how best to build customer-centric platforms and products to create a truly viable business proposition. Given that each market is unique, taking the time to understand and analyze social, economic and cultural factors will help immensely in developing appropriate products that address customer pain points and meet customer needs.

Source- https://www.ifc.org DIGITAL ACCESS: The Future of Financial Inclusion in Africa What developing countries can teach America about banking; https://edition.cnn.com/



## “የፈርጦቹ ጉዞ”

ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ፣
የፈርጦቹን ትርክት ከልቡ ያኖረ፣
ገና ከጅማሮ ከአመታት በፊት፣
የባንክ ኢንዱስትሪው ሳይመጣ ወደፊት፣
ጥቂት ባለራዕዮች ብሩህ ተስፋን ይዘው፣
ድንቅ አሻራ አኖሩ የዛሬን አስበው፡፡
የአዋሽ ኢንሹራንስ እንዲሁም ባንካችን፣
ውጥኑ ሲያፈራ ሲታይ ስኬታችን፣
ቢነገር ቢዘከር ከቶ ያሰኛል ፈገግ፣
መች ተነግሮ ያልቃል የእህት አማቾቹ ወግ፡፡
በፋይናንስ ዘርፉ ቀድሞ ፋና ወጊ፣
የህይወትን ዋስትና ፍጹም አረጋጊ፣
ዘመን ቢቀያየር አብረው እየዘመኑ፣
አንጋፋ ተብለው ሀገር እያቀኑ፣
ሀያ አምስት አመታት ወደፊት ነጎዱ፣
በአዋሽ ተሰይመው ድህነትን ናዱ፡፡
ችግር ተግዳሮትን በድል ተወጥታችሁ፣
የዚህ ድል ሀዋርያት እንኳን ደስ አላችሁ፡፡
ተደሰች ሀገሬ አሁን ቀን ወጣልሽ፣
ማሳው እንዳበበ እንደለማ በአዋሽ፣
መላ ለቸገረው ብልሀትን አሳሽ፣
ለውድ ደንበኞቹ ሁሌም ፈጥኖ ደራሽ፣
ከልብህ አድምጠኝ ይልቅ ምክር ልስጥህ፣
የስኬት መፍቻ ቁልፍ ሚስጥሩን ላብስርህ፣
ሳትደክም ሳትሰለች ከአዋሽ ጋር ከሰራህ፣
እድል ካንተ ጋር ነች ያለአንዳች ኪሳራ፡፡

ሰላም ተክለፅዮን
(ማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
አዋሽ ባንክ)

## Proverbs

“The ultimate value of life depends upon awareness and the power of contemplation rather upon mere survival.”(Aristotle)

“Fear is the source of superstition, and one of the main source of cruelty. To conquer fear is the beginning of wisdom.” Bertrand Russell)

“At its core, banking is not simply about profit, but about personal relationships.” (Felix Rohatyn)

“Good banking is produced not by good laws, but by good bankers.”( Hartley Withers)

አዋሽ ባንክ
AwashBank

ikhlas
Nurturing like the river

# ከወለድ-ነፃ
# የባንክ አገልግሎት

## ይጠቀሙበት!
## አማራጩን ይወዱታል!!

አዋሽ ባንክ
# AwashBank
Nurturing Like the River

## ከታወቁ ዓለም አቀፍ የሐዋላ አገልግሎት ሰጪ ወኪሎች በኩል ገንዘብ ለመቀበል ምቹና ቀልጣፋ ባንክ



XPRESS MONEY simple. fast. safe

Moneytrans

MONEY EXCHANGE

worldremit

WESTERN UNION MONEY TRANSFER

XOOM A PayPal Service

S.W.I.F.T. AWINETAA

mfi

بنك الدوحة DOHA BANK

TFS money transfer

SEND EXCHANGE ارسال للصرافه

Trans-Fast WORLDWIDE MONEY TRANSFER Money Transfer You Can Trust!

AME Asgori Money Express Transfer on the spot

Ria Worldwide Money Transfer

EzRemit The Reliable Online Money Transfer Service

Dubai Remit Global Money Trasnfer

الأنصاري للصرافة AL ANSARI EXCHANGE 2017

Dahabshiil Fast Money Transfer you can trust www.dahabshiil.com

MoneyGram.



# Photo Reel





AB's & AIC staff participated on blood donation for the 25th year anniversary






AB's & AIC staff engaged in planting trees for 25th year anniversary



Opening ceremony of 'Ikhlas' new interest free banking branches



AB's and Amref Health Africa partnership celebration at Belay Zelek primary school



አዋሽ ባንክ

AwashBank

Nurturing Like The River

The Bank that
# NURTURES
Your Life!

